# መጽሓፉን ገለጥ አድርገው ያንብቡ፣ ቁም ነገሩን ያላምጡ!

November 3, 2009

<u>መንከባከብና ማስወገድ ያለብን ባህሎች</u> የተሰኘውን መጽሓፍ ከደረስኩ በኋላ ብዙ ኢትዮጵያውያን አንብበው ጠቀሜታ አስተያየት፡ ምላሽና አቃቂር የላኩልኝ አሉ። ለነዚህ ሁሉ ወገኖች ምስጋናየ እጅግ በጣም የላቀ ነው። ነገር ግን አንድ አንድ ኢትዮጵያውያን መጽሓፉን ከማንበብ ይልቅ በወሬና አሉቧልታ ተታለው ላለማንብብ መወሰናቸውን ስሰማ ገርሞኝ የመጽሓፉ ይዘትና መልእክት ሳይገነዘቡ ቀርተው ይሆን በማለት በአእምሮየ ሳሰላስል ቆይቻለሁ። ግን ደግሞ፡ ባያነቡትም ቀረብ ብለው ሽፋኑን ብቻ ብያዩት እንኳ የመጽሓፉን ይዘት አስመልክቶ መላምት ያገኙ ነበር ብየም ከአንዳንድ ሰዎች ጋር ተነጋግሬ ነበር። ይኸም ያልኩበት ምክንያት በመጽሓፉ ሽፋን ላይ ይህ መልእክት ሰፍሯል፦

በሽፋኔ አትፍረደኝ
ገልጠህ አንብበኝ
ሃሳብ ካለህ ግለጥልኝ
ገንቢ ነቀፌታ አቅርብልኝ

አሁን በቅርቡ የተረዳሁት ነገር ቢኖር ግን ለካ አንዳንድ ተንኮለኞች መጽሓፉ እንዳይነበብ ዘመቻ ሲያካሂዱ ሰንብተዋል። ኃላቀርነት እጅግ በጣም ክፉ ጠላት ነው! ዝርዝሩን ከዚህ በታች አጠር መጠን ባለ ሁኔታ አቅርቤላችኋለሁ፦

ይህ ጽሑፍ ለኢትዮጵያ ሕዝብ በይፋ ማቅረቡ አስፈላጊ ሆኖ ያገኘሁት ሁለት ተቃራኒ ስብስቦች የኔን ስም በመጥቀስና በተለያዩ ጊዜያትና በልዩ ልዩ መድረኮች የወያኔ አባል መሆኔን ለመግለጽ ስለሞከሩ ነው። ተቃራኒ ስብስቦች ያልኳቸውም ምክንያት በመርሕና በዓላማ የማይገናኙ ሆነው፡ ግን በማወቅም ባለማወቅም አንድ ዓይነት የፖለቲካ ዘመቻ በማካሄዳቸው፣ በቀጥታ ሕዝቡን ለማደናገር መቻላቸው፣ ኢቀጥታዊ በሆነ መንገድም አሁን በስልጣን ለሚገኘው የኢትዮጵያ መንግስት ገጸ በረከት መለገሳቸውን ነው።

ስብስቦቹ፡ 1) የትግራይ ተወላጆች ሆነው በተለይም ለኢሕአዴግ መንግስት በካድሬነትና ጋሻ ዣግሬነት የሚያገለግሉና በዚሁ ስራቸው ተሰማርተው ደግሞ ትርፍና ጥቅም የሚያገኙ፣ 2) የትግራይ ተወላጆች ያልሆኑ ኢትዮጵያውያን፣ የጠራ የፖለቲካ አጀንዳ የሌላቸው፣ ካለው መንግስት ጥቅም ባያገኙም ሳያውቁት ግን የመንግስቱን ፍላጎትና ጥቅም ያራመዱ፡ ናቸው።

ከብዙ ጊዜ በኋላ፡ በጥናትና ምርምር በሁለቱ ስብስቦች የተሰማሩና ስም የሚያጠፉ ግለሰቦች ማን መሆናቸውን ደርሸበታለሁ። በዚሁ ጽሑፍ ግን ባሁኑ ወቅት ስማቸውን በዝርዝር ማስቀመጡ አስፈላጊ ሆኖ አላገኘሁትም። የዚሁ ጽሑፍ ዋና ዓላማ በሚካሄደው መሰሪ የስም ማጥፋት ዘመቻ የኢትዮጵያ ሕዝብ የተሳሳተ ማስረጃ እንዳይኖረውና ኢርትዓዊ ግንዛቤ እንዳያደርግ እንጂ እኔ ቅር ስላለኝ አይደለም።

የኔ ዓላማና ፍላጎት፡ እንዲሁም የትግል ጉዞና አቅጣጫ ምን እንደሆነና ምን እንደሚመስል በርካታ ኢትዮጵያውያን ከጽሑፎቼ በመገንዘብና በመረዳት፡ በተለያየ ጊዜ ጠቃሚ አስተያየትና ምላሽ ሰጥተውኛል። ሰፊው ሕዝባችን ደግሞ ዋና ዓላማየና ፍላጎቴ በተቀዳሚ የኢትዮጵያ አንድነትና ሉዓላዊነት፡ ባገራችን ዴሞክራሲ እንዲሰፍን፡ ኢትዮጵያችን እንድትለማና እንድታብብ፡ ሕዝባችንም ከረሐብና ከቸነፈር እንዲላቀቅ፡ መሆኑን እንደሚያውቅልኝ የጸና እምነቴ ነው።

እንድያውም ይኸንን አጋጣሚ በመጠቀም ለአንባብያን ማስታወስ የምፈልገው ነገር ቢኖር ስብስቦቹ በሚያደርጉት የውስጥ ለውስጥ ዘመቻ ተደናግረው፡ ከፍ ብየ ከጠቀስኳቸው ዓበይት የኢትዮጵያ ጥያቄዎች ትኩረታቸው እንዳይጨናገፍ ነው። እስካሁን ድረስም ለስብስቡ ፕሮፓጋንዳ በትዕግስት ማሳለፍ የፈለግኩት በእንካ ስላንትያ ገብተን ለረጅም ጊዜ የታገልንበትና የገፋንበት ዓላማ መንገድ እንዳይስት ከሚል ፍራቻ ነበር። አሁን ግን፡ አቋሜን ግልጽ እስካደረግኩ ድረስ፡ በመጠኑም ቢሆን ማብራርያ መስጠቱ አይከፋም ከሚል አንጻር ነው ይኸንን መግለጫ ለማውጣት የተገደድኩት።

የሁለተኛው ስብስብ ዘመቻ በቅርቡ የጀመረ ሲሆን የጋሻ ዣግሬው ስብስብ ግን የቆየ ሆኖ የያዘው ስልት ደግሞ ወያኔ ስልጣን ከመያዙ በፊት ሲጠቀምበት ከነበረ እኩይ ተግባር ተቀጥያ ነው። ለምሳሌ ያህል በ ‘ኢትዮጵያ ይንጋልሽ’ የተደረሰው ጽሑፍ መጥቀሱ በቂ ይሆናል። ጸሐፊው ባቀረበው ዘገባ ለአንባቢ ሁሉ ዘግናኝ ነበር፣ ወያኔና ካድሬዎቻቸው ከተጠቀሙበት አንዱን ስልት ደግሞ በዚሁ መልክ ያስቀምጠዋል፦ ወያኔ የትጥቅ ትግል በሚያካሂድበት ጊዜ አንዳንድ የሽምቅ ተዋጊዎቹን ሆን ብሎ ለደርግ እጃቸውን እንዲሰጡ ያደርግና በነዚሁ ተዋጊዊች ኪስ ውስጥ ደግሞ በልዩ ልዩ የኢትዮጵያ ከተሞች ለሚኖሩ የትግራይ ተወላጆች ግን ጸረ-ወያኔ የሆኑትን የስም ዝርዝር ይከታል። እጃቸውን ለደርግ ከሰጡ በኋላ፡ የደርግ አባላት ይፈትሿቸውና ‘ይህ ምንድ ነው’ ብለው ሲጠይቋቸው፡ ‘በከተማ የሚገኙ የደጋፊዎቻችን ስም ዝርዝር ነው’ ብለው ይመልሳሉ። የዋሁና ደንቃራው ደርግ ደግሞ ምንም ዓይነት ምርምር ሳያካሂድ ሚስኪኑን የትግራይ ተወላጅ ይለቅምና በእስር ቤት ይወረውራል፡ ይገድላል። በዚሁ ረገድ ወያኔዎች ያልደገፏቸውን ወይም የተቃወሟቸውን የትግራይ ልጆች በደርግ እጅ እንዲጠቁ አድርጓል።

ጋሻ ዣግሬዎቹ የኔን ስም በማጥፋት የሚያከሂዱት ዘመቻ ደግሞ ከዚሁ ‘ኢትዮጵያ ይንጋልሽ’ ካቀረበልን ዘገባ እጅግ በጣም ተመሳሳይ ነው። ካድሬዎቹ በቅርቡ በሆነ ጉዳይ ተገኝተው “ፕሮፌሰር ገላውዴዎስ መሪያችንና አባላችን ነው” በማለት ተሰብስበው ለነበሩት ኢትዮጵያውን ለማደናገር ሞክሯል። የሚገርመው ግን ሁለተኛው ስብስብም ሳያውቀው ከካድሬዎቹ እጅና ጓንቲ በመሆን ‘እነ ገላውዴዎስ ወያኔዎች ስለሆኑ ተጠንቀቁላቸው’ የሚል ሐሰት አናፍሷል። እኔ የወያኔ አባል ሆኜ አላውቅም፣ ምልአተ ሕዝቡም ያውቃል። ይሁንና የተደናገሩና የተታለሉ ያገር ወገኖች፡ ቍጥራቸው አነስተኛ ቢሆንም ቅሉ፡ ሓቁን ማወቅ ግን አለባቸው የሚል እምነት አለኝ።

ስብስቦቹ በአመሪካና በአውሮጳ ቢገኙም ቅሉ፡ በተለይ ግን በዋሽንግተን ዲሲ፡ ኒው ዮርክ፡ ሺካጎ፡ ቦስተን፡ በይ ኤርያ፡ እና ሎስ አንጀልስ አከባቢ ይገኛሉ። ስብስቦቹ የኔ ስም አጠፉ አላጠፉ እኔ ከዓላማየ ፍንክች አልልም። ኢትዮጵያ-አቀፍ የፖለቲካ አጀንዳ ከዚህ ቀደም፡ አሁንም፡ ለወደፊትም የማራምደውና የምታገልለት ተቀዳሚ ዓላማየ ነው። ይህ እስከሆነ ዘንዳ ለአንባቢ በተለይ፡ ለሕዝቡም ባጠቃላይ ማስታወስ የምፈልገው ነገር ቢኖር የሚናፈሰው ሐሰትና ሆን ብሎው የሚበተኑትን (በጽሑፍም በቃልም) ከፋፋይ የፖለቲካ ስልቶች ቀኖናዊ በሆነ መንገድ እንዳይቀበላቸው ነው። ፕሮፓጋንዳዎቹን ከማላመጡ በፊት ሕዝቡ ቢያንስ ቢያንስ መጠየቅና መመራመር ይኖርበታል። ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ነጻ በሆነ መንገድ መጻሕፍትና ልዩ ልዩ ጽሑፎችን ማንበብ ይኖርበታል። ታዋቂው አፍሪቃዊ-አመሪካዊ ፍረደሪክ ዶግላስ "ማንበብ ስትጀምር ለዘልዓለም ነጻ ትሆናለህ" በማለት ወገኖቹን እንድያነቡ ያደፋፍራቸው ነበር።

እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ በጎሊናው እንጂ በግለሰቦች ብቻ ተመርቶ ፍርድና ትችት መድረስ የለበትም። ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ለሕዝቡና ለሃገሩ ቢቻል መስዋእት መሆን፣ ባይቻል ደግሞ መቆርቆር የሚጠበቅበት ይሆናል። ስለሆነም የመጀመርያ ተግባሩ ኢትዮጵያን የሚጎዳ ማንኛውም አጀንዳ መታገል ነው፣ ይህም አስተዋይነትና ብልህነት ብቻ ሳይሆን፡ ቍርጠኝነትና ነጻ አስተሳሰብን የሚጠይቅ ነው። በተግባር ለማዋልና ስኬታማ እንዲሆን ከተፈለገ ደግሞ ከጎሳ ፖለቲካና አሉቧልታ እንዲሁም ከጠባብ አመለካከትና ጥቅሞች ነጻ መውጣት ቅድመ-ሁኔታ ይሆናል። የኢትዮጵያ አንድነት፡ ሉዓላዊነት፡ ነጻነትና ብሔራዊ ጥቅም የምናስጠብቀው በሃገር ፍቅርና በላቀ አመለካከት ሆኖ ሕብረታችን ደግሞ እንደ አለት የጸናና ጠላት በቀላሉ የማይሸረሽረው ሲሆን ነው። የኔ ፍላጎትና እምነት የኢትዮጵያን ጥቅም ከሚያራምዱ ዓበይትና አንገብጋቢ ጥያቄዎች ጋር የተቆራኙ ናቸው። ወሬና አሉቧልታ የኢትዮጵያን ጥቅም የሚያደናቅፉ ስለሆኑ ነው ደግሞ የስብስቦቹ ሰለባ እንዳትሁኑ አደራ የምለው። የኔ ስምስ ምንም አይደለም ቢያጥላሉትና ቢያጠፉት። ነገር ግን ይኸንን እኵይ ተግባራቸውን እንደ ስልት ተጠቅመው የኢዮጵያን ጥቅም የሚጻረሩ ከሆነ ግን ዝም ብለን የምናያቸው አይሆንም፣ ድር ብያብር አንበሳን ያስር ነውና ለሁሉ አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ በአንድነቱ እንዲጸና አደራ እላለሁ። ስለሆነም መጽሓፉን ገለጥ አድርገው ያንብቡ፣ ቁም ነገሩን ያላምጡ!

ከማክበር ሰላምታ ጋር
ገላውዴዎስ ኣርኣያ ዶ/ር

All Rights Reserved. Copyright © IDEA, Inc. 2009. Please contact webmaster@africanidea.org for constructive feedback.